# ዴሞክራሲያ

የኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ ልሳን

ዴሞ ቅጽ 45 ቁጥር 3 የካቲት 2012 ዓ.ም.


## አገራችን የምትገኝበት የቀውስ ሁኔታና  መፍትሔው

በረጅሙ የአገራችን ታሪክ ውስጥ በየካቲት ወር የተፈጸሙ መልካምም መጥፎም ክስትቶች አሉ። የሩቆችን ትተን የቅርቦችን ብንወስድ እንኳ በየካቲት 23 ቀን 1888 ዓ.ም. ኢትዮጵያውያን በጣሊያን ጦር ላይ የተቀዳጁት አንፀባራቂ ድል በአገራችን ብቻ ሳይሆን በዓለም ሕዝብ ዘንድ የጥቁር ሕዝብን አስደናቂ ጀግንነት ያስመሰከረ ክስተት ሲሆን በየካቲት 12 ቀን 1928 ዓ.ም. የፋሽስቱ የግራዚያኒ ጦር በአዲስ አበባና በአካባቢው ነዋሪ በሆኑ ኢትዮጵያውያን ላይ ለሶስት ተከታታይ ቀናት ያካሄደው አረመናዊ የዘር ማጥፋት ጭፍጨፋ ደግሞ ኢትዮጵያውንም ሆኑ የዓለም ሕዝቦች ምንም ጊዜም በአንክሮ የሚያስታውሱት አሳዛኝ ክስተት ነው። በዚህ ወር ኢትዮጵያውያን የካቲት 12ን በሀዘን ያስታወሱበት የአድዋን ድል ደግሞ በደስታ የዘከሩበት በመሆኑ በዚህ የዴሞክራሲያዊ ዕትም ስለ ሁለቱም አንስተን ለመተንተን አንቃጣም። የዛሬ አርባ ስድስት ዓመት በአገራችን የተከሰተው ሌላው ክስተት የየካቲት 66 ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ሲሆን በአገራችን ታሪክ ውስጥ ጎላ ያለ ሚና ያለው ነው። ዛሬ አገራችን ለገባችበት አሳዛኝና አስጊ ሁኔታ በተመሳሳይነትም ሆነ በልዩነት፣  ማሳያና ማነጻጸሪያ እንዲሁም ትምህርት መቅሰሚያ ሊሆን ስለሚችል ይህን የታሪክ ክስተት እንደመግቢያ በአጭሩ አንስተን ወደ ዋናውና ወደ ወቅቱ የአገራችን የፖለቲካ ሁኔታ እናልፋለን።

የየካቲት 66 ቱ  ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ለረጅም ዘመናት በሕዝብ ላይ በርካታ በደሎች ሲያደርስ የነበረውን የአጼውን ሥርዓት የገረሰሰ የሕዝባዊ ትግል ውጤት ነው። የተማሪዎችና የለውጥ ፈላጊዎች የመሬት ለአራሹ ጥያቄ፤ የታክሲ ነጂዎች አድማ፤ የነገሌ ቦረና የወታደሮች አመጽ፤ የባንክ የመምህራንና የሌሎች ሠራተኞች የሥራ ማቆም አድማ፤ የእስልምና ሃይማኖት ተከታዮች የእኩልነት ጥያቄ የየካቲቱ 66 ቱ እንቅስቃሴ አካል የነበሩ ሲሆን እንቅስቃሴው በሂደት ስፋትና ጥልቀት አግኝቶ የብሔርና የሴቶች እኩልነት፣ የሃይማኖት ነጻነትና እኩልነት፣ የሰብአዊና ዴሞክራሲዊ መብቶች፣ እንዲሁም የሕዝባዊ መንግሥት ጥያቄዎችን አንግቦ ተነስቷል። ይህ የመላው የኢትዮጵያን ሕዝብ ድጋፍ ያገኘ እንቅስቃሴ የአፄውን ሥርዓት አንኮታኩቶ ለመጣል ቢችልም ሕዝብን ለሥልጣን የሚያበቃና  የሚያስተባብር የጠነከረ ድርጅት ባለመኖሩ ሥልጣን በባለቤቱ በሕዝብ እጅ ሳይገባ በፋሽስታዊ ወታደራዊ ቡድን ሊጠለፍ ችሏል። የየካቲቱ ሕዝባዊ እንቅስቃሴን የተለየ ባህርይ የሚሰጠው ኢትዮጵያውያን በጾታ፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በብሔረሰብ፣ በዕድሜ ሳይለያዩ በአንድነትና በኅብረት ለዘመናት ጨቋኝ  የነበረውን ሥርዓት ለማስወገድ መታገላቸው ነው። የሙስሊሙ ኅብረተሰብ ለሃይማኖት እኩልነት ድምጹን ሲያሰማ የክርስቲያን ምዕመናን ከጎናቸው በመሆን ድጋፋቸውን ገልጸዋል፤ ለሠራተኞችና ለታክሲ ነጂዎች ትግል ተማሪዎች አጋር ሆነው ታግለዋል፤ ለሴቶች እኩልነት ወንዶች፣ ለብሔርና ብሔረሰብ እኩልነት የሁለም ብሔረሰብ አባላት በግምባር ቀደምትነት በአንድነት ድምፃቸውን አሰምተዋል። ይህ በኢትዮጵያያዊነትና በአብሮነት እጅ ለእጅ በመያያዝ የተካሄደው

ትግል ኢትዮጵያውያን በቋንቋና በሃይማኖት፣ በብሔር እና በመኖሪያ አካባቢ ቢለያዩም በሺ ክሮች ተጋምደው ለሺ ዓመታት አብረው የኖሩ መሆናቸውን ያረጋገጣል። የየካቲቱ አብዮት ዋናና መሠረታዊ የሆነው የሕዝብ ጥያቄ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ይቋቋም፤ ይህንንም እውን ለማድረግ ሁሉንም ፓርቲዎች፣ ቡድኖች ፣ የሙያ ማኅበራት፣ ሕዝባዊ አካሎች ወዘተ... የሚያካትት ጊዜያዊ ሕዝባዊ መንግሥት ይቋቋም የሚል ሆኖ ሳለ ኃይሉን ተቆጣጥረው የነበሩ ክፍሎች የሕዝቡን ጥሪ ወደ ጎን አድርገው የራሳቸውን ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት አቋቁመዋል።

የዛሬ 46 ዓመት በኢትዮጵያ ምድር እውን የሆነው የየካቲት 66 ሕ ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ያነሳቸው ዋና ዋና ጥያቄዎች ሙሉ በሙሉ እውን ሳይሆኑ በየምዕራፉ ሥልጣን በያዙ ቡድኖች ተደፍጠጠው ይኸው እዚህ ደርሰናል። ለ 27 ዓመታት በአምባገነነት በሥልጣን ተሰይሞ የነበረውን የወያኔውን ቡድን ለማስወገድ ውስጥ ውስጡን ሲካሄዱ የነበሩ ሕዝባዊ ትግሎች በመጨረሻዎቹ ሶስት ዓመታት ተጠናክረውና ጎልተው በመውጣት የወያኔን ቡድን ማንበርከካቸው ይታወቃል። ወያኔ በሕዝብ ትግል ተንበርክኮ፤ ጥፋተኛ እንደነበር ምሎና ተገዝቶ አካሂድኩት ባለው የጥገና ለውጥ እንቅስቃሴ የሕዝቡን ትግል ጠልፎ አጨናግፏል። ባለፉት ዓመታት ሕዝባዊ ትግሎች የተካሄዱት፤ በርካታ ወገኖች መስዋዕትነት የከፈሉት ለሥር ነቀል ለውጥና ሕዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት ሆኖ ሳለ አዲስ ጠቅላይ ሚኒስትር ተብየውን በመሾም የተደረገው የጥገና ለውጥ እንቅስቃሴ ሥልጣንን ከወያኔ ወደ ኦህዴድ/አዴፓ ከማሸጋሸግ በስተቀር ለሕዝቡ ምንም የፈየደው የለም። እንዲያውም አገራችንን አሁን ለምትገኝበት ምስቅልቅል ሁኔታ ዳርጓታል።

በአሁኑ ወቅት አገራችን እጅግ አሳሳቢ ሁኔታ ውስጥ ትገኛለች። የመኖር ነፃነት መገፈፍ፤ የጽንፈኛ ብሔረሰቦች መግነን፤ የቡድን፣ የብሔርና የጎሳ መብት ከሌላው ገንኖ መታየት፤ የሃይማኖት ክፍፍልን የሚገፋፉ ሴራዎች መጠናከርና መስፋፋት፤ የክፍፍልና የጥላቻ ፖለቲካ መሰራጨት፤ የሥርዓት አልበኝነት መግነን፤ የአስተዳደርና የፍርድ አካላት መዳከም፤ የፀጥታና ወታደራዊ ተቋሞች ለጽንፈኛ ብሔርተኞች ሰርጎገብነት መጋለጥ በጉልህ ከሚታዩት ችግሮች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ ናቸው። ወንጀል ተከላካዮች ወንጀል ሠሪዎች ሆነዋል። በገዥው ክፍል ውስጥ ያለው ክፍፍል፤ የወያኔ ቡድን አፍራሽ እንቅስቃሴ፤ የኦህዴድ የበላይነት መጠናከር፤ በአንዳንድ አካባቢዎች የሚታየው ጦርነት እና አገሪቱን ተብትበው የያዙ ሌሎች ጎላ ጎላ ያሉ ችግሮች ወደ እርስ በርስ ግጭት የሚወስደውን ጎዳና እያመቻቹ መሆኑ በጉልህ እየታየ ሲሆን ወቅታዊና ሁለገብ መፍትኄ ካላገኙ ኢትዮጵያ እንደአገር የምትቆይበትን ህልውና እየተፈታተኑ ለመሆናቸው አጠራጣሪ አይደለም።

ዛሬ በአገራችን ውስጥ የመኖር ነጻነት ተገፏል። በአንድ አካባቢ በሰላም ለመኖር፤ ወያም ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ለመንቀሳቀስ አዳጋች መሆኑ እየታየ ነው። በቅርቡ በደምቢዶሎ በጽንፈኛ የብሔረሰብ ቡድኖች የታገቱት በእድሜ ለጋና አብዛኞቹ ሴቶች የሆኑት የአማራ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ደብዛቸው ጠፍቶ ለወላጆቻቸው ሰቀቀን ሆነዋል። የአገዛዙ ባለሥልጣኖች እንኳን እንዲህ ዓይነቱን አረመኔያዊ ተግባር አስቀድመው ሊከላከሉ ይቅርና የተማሪዎችን አፈና አንድ ጊዜ አላወቅንም ሌላ ጊዜ ተፈተዋል፤ አንዴ ደግሞ እያጣራን ነው የሚሉ የተምታቱ መግለጫዎች በመስጠት በወላጆች ቁስል ላይ እንጨት ሲሰዱ ቆይቷል። በአማራው አካባቢ ከ 10 ዓመት በታች የሆኑ ደሃ ህጻናት ከብት ሲጠብቁ ታፍነው ተወስደው የገንዘብ ካሳ ተጠይቆባቸዋል፤ ቤተሰቦች መክፈል ሲያቅታቸው አረመኔያዊ በሆነ መንገድ ታርደዋል። ዜጎች በሚናገሩት ቋንቋና በማንነታቸው እየተለዩ በታጠቁ ኃይሎችና በቡድን በተደራጁ መንጋዎች ጥቃት ደርሶባቸዋል፤ አካላቸው ተጎድቷል፤

ከቀያቸው ተፈናቅለዋል። በዩኒቨርስቲዎች ተማሪዎች ከአንዱ ወይም ከሌላ ብሔር በመሆናቸው ብቻ በርካታዎች ተገድለዋል፤ ተደብድበዋል። ዛሬ ከአካባቢዎች ውጭ ባሉ ዩኒቨርስቲዎች ውስጥ የሚማሩ ተማሪዎች የሚደርስባቸውን የህይወትም ሆነ የአካል ጥቃት በመስጋት በሰከነ አዕምሮ ትምህርታቸውን መከታተል ተስኗቸዋል። የሃይማኖት ተቋሞች - ቤተ ክርስቲያናት መስጊዶች- ተቃጥለዋል፤ የምዕመናን ንብረቶች ወድመዋል፤ ዜጎች በእምነታቸው ብቻ ተገድለዋል፣ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፤ ከኖሩበት ቦታ ተሰደዋል። በአንድ ወቅት አገራችን በዓለም ላይ በአገር ውስጥ በተሰደዱ ስደተኞች ብዛት ቀዳሚውን ስፍራ ይዛ እንደነበር እናስታውሳለን።

የእነዚህ ሁሉ ቀውሶች ጠንሳሾችም ሆነ አራማጆች በሚገባ የታወቁ ናቸው። አንደኛው ወያኔ፣ ሁለተኛው የጽንፈኛ ብሔረተኛ ቡድን፣ ሶስተኛው ደግሞ በሥልጣን ላይ ያለው ክፍል ነው። የወያኔ ቡድን ለ 27 ዓመታት ያህል የዘረፈውን የኢትዮጵያ አንጡራ ሀብት፤ የመለመለውን የሰው ኃይልና ያከማቸውን የጦር መሳሪያ በማንቀሳቀስ በተለያዩ የአገራችን ክፍሎች ውስጥ የሚያካሂደውን ማተራመስ ቀጥሎበታል። ባለፉት ሁለት ዓመታት በተለያዩ አካባቢዎች ብሔርና ቋንቋን መሠረት አድርገው የተካሄዱ ግድያዎች፤ መፈናቀሎችና የንብረት መውደሞች ከጀርባቸው የወያኔው ቡድን ያለበት መሆኑ የማይካድ ነው። በመጀመሪያዎቹ ወቅቶች በኦሮሞና በሶማሌ ብሔረሰቦች መካከል የተካሄደው ጥቃት ግድያና መፈናቀል ለአብነት የሚጠቀስ ነው። በየዩኒቨርስቲዎች በተማሪዎች መካከል ለተካሄዱ ግድያዎችና አፈናዎች፤ ለዕምነት ተቋሞች መቃጠል፤ ለምዕመናን ግድያዎች፤ ለሕገ ወጥ መሳሪያ ዝውውር ወዘተ... ከሥልጣን የተገፋው ወያኔ እጅ ያለበት መሆኑ አጠያያቂ አይደለም። ሌሎቹ ከውጭ ተጋብዘው ገብተው እንዳሻቸው የሚጨፍሩ ብሔረተኛ ድርጅቶች ናቸው። በግለሰብ ሆነ በቡድን፤ በቀጥታ ሆነ በተዘዋዋሪ አንዱን ብሔረሰብ በሌላው ላይ የአንዱን ሃይማኖት ተከታይ በሌላው ላይ በማነሳሳት በሕዝብ ውስጥ ግጭቶች እንዲፈጠሩ፤ ግድያዎችና እንዲፈጸሙ የአካል ጉዳቶች እንዲደርሱ የሕዝብ መፈናቀል እንዲከሰት አድርገዋል። በዋናው ከተማ በአዲስ አበባ፣ በለገጣፎና በቡራዩ፣ በሀረር በአርሲና በባሌ፣ በሸዋ አጣየና፣ ማጀቴ፣ በጉጂ ዞን በጌዲዮ ተወላጆች ላይ የደረሰው ግድያና መፈናቀል፤ በቤኒሻንጉል ጉምዝ የተፈናቀሉ የኦሮሞ የአማራ ተወላጆች፤ በዝዋይ ከተማ በወላይታ ተወላጆች ላይ የደረሰው ብሔር ተኮር ጥቃት፤ በጋምቤላ የደረሰው የዜጎች መፈናቀል ሁሉም በብሔርተኛ ድርጅቶች ገፋፊነት የተደረጉ የሽብር እንቅስቃሴዎች ናቸው። የጽንፈኛ ብሔረተኛ ቁንጮ የሆነ ግለሰብም በማኅበራዊ ሚዲያ ባካሄደው ቅስቀሳ በአጭር ጊዜ ውስጥ ተከታይ መንጋዎችን በማሰማራት ከ 86 በላይ ዜጎችን ማስገደሉን እናስታውሳለን። በሥልጣን ላይ ያለው የጠቅላይ ሚኒስትር ተብየው ቡድንም በአገሪቱ እየተካሄደ ለሚገኘው የጸጥታ መደፍረስና በጉልህ ተከስቶ ለሚታየው ምስቅልቅል ሁኔታ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በኃላፊነት የሚጠየቅ ነው። በወለጋ ታጥቀው በሚንቀሳቀሱ የኦነግ ሸኔ አባላት ላይ እየተወሰደ ያለው እርምጃ፤ በኦሮሞ የብሔረሰብ ድርጅቶች መካከል የሚታየው ሽኩቻና ወደ ደም መፋሰስ እየሄደ ያለው እንቅስቃሴ አገሪቱን ወደ ባሰ ብጥብጥና ቀውስ ሊወስዳት እንደሚችል እየታየ ነው። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ የተለያዩ ውስብስብ ችግሮች በየቀኑ እየተቀፈቀፉ፤ እንደአሸን እየበዙ በሄዱበት ሁኔታ ምርጫ የሚባለው ቧልት ታቅዶ ሕዝባችንን ለበለጠ ቀውስ እና ደም መፋሰስ እየጋበዘ ይገኛል። በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች የጸጥታው ሁኔታ ባልተረጋጋበት፤ ጽንፈኞች ትናንሽ ንጉሦች ሆነው በመንጋ እየተደራጁ የሕዝብን ኑሮ በሚያውኩበት ሁኔታ እንዲሁም በተለያዩ ክፍሎች መካከል በጉልህ የሚታየው ልዩነት በውይይትና በድርድር መፍትኄ ባለገኘበት ሁኔታ የሕዝብ ቆጠራ ሳይካሄድና ያውም የክረምቱ ዶፍ በሚበረታበት በነሐሴ ወር አገራዊ ምርጫ እንዲካሄድ ማቀድ አገሪቱን ለእርስ በርስ ጦርነት መዳረግ መሆኑ ግልጽ ነው። ዛሬ ዜጎች ከዳር እስከ ዳር የአገራቸው ሉዓላዊነትና

አንድነት እያሳሳባቸው መጥቷል። ፍርሃት፤ ስጋት ጭንቀት ነግሶባቸዋል። ሥልጣን በያዘው ቡድን ሙሉ በሙሉ ተስፋ በመቁረጣቸው የታያቸው ብቸኛው አማራጭ ወደ ፈጣሪ ልመና ማቅረብ ብቻ ሆኗል።

መፍትኄው ምን ሊሆን ይችላል የሚለው በሁሉም አእምሮ ውስጥ የሚብሰለሰል ጥያቄ ነው። ረጅም ታሪክ ያለት አገራችን ህልውናዋን ጠብቃ እንደ አገር ልትቀጥል የምትችለው ሉዓላዊነቷ ሲከበርና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ላይ የተገነባ የሕዝብ አንድነት እውን ሲሆን ብቻ ነው። ለዘመናት በሺ ክሮች የተሳሰሩና የተጋመዱ በአንድነት በመኖሩ ረጅም ታሪክ ያላቸው ከ 80 በላይ የሚሆኑ ብሔረሰቦቿ አንደነታቸውን እንደ ብረት አጠንክረው መኖር የሚችሉት ተብትበው የያዟቸውን የችግሮች ምንጮች ነቅሰው በማውጣት፤ በግልጽ ተወያይተው ተደራድረውና በመፍትኄዎቹ የጋራ ሕግና አብሮ የመኖር ሥርዓት ለመቅረጽ ሲችሉ ብቻ ነው። ለዚህም ከአምባገነን ሥርዓት ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚያሸጋግር የሽግግር ሂደት እውን ማድረግ የግድ ነው።

ኢሕአፓ አገሪቱን ተብትበው ለያዟት ውስብስብ ችግሮች መፍትኄ ይሆናል በሚል የሚያቀርበው የሽግግር ሂደት ሀሳብ እኛ እናሻግራችኋለን በማለት ሲመጻደቅ የቆየው ጠቅላይ ሚኒስትር ተብየውም ሆነ ይህን ተቀብለው ሽግግር እየተደረገ ነው በማለት ቀንና ማታ የሚያደነቁሩን ደጋፊዎቹ ከሚያቀነቅኑት የሽግግር ዓይነት በጣም የተለየ ነው። ላለፉት ሁለት ዓመታት ራሳቸውን ተፎካካሪ ፓርቲ በማለት የሚጠሩት እነዚህ ክፍሎች በተወሰዱት አንዳንድ የጥገና ለውጥ እርምጃዎች ረክተው እስከ ምርጫ ያለውን ጊዜ እንደ ትክክለኛ የሽግግር ሂደት በመቁጠር ችግሮቹ ሁሉ በሚቀጥለው አገራዊ ምርጫ ይፈታሉ በሚሉ የህልም ሩጫ ውስጥ ሲባዝኑ ቆይተዋል። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ አንዳንዶቹ የጥገናው ለውጥ በአገሪቱ ውስጥ ቀውስንና ችግርን ከመቀፍቀፍ በስተቀር ሰላምንና ጸጥታን ሆነ የተሟላ ዴሞክራሲን እውን ማድረግ የማይችል መሆኑን ሲረዱ የቀድሞ ዘፈናቸውን ትተው አዲስ ዘፈን መዝፈን ጀምረዋል። ይሁን እንጅ ሽግግሩ ተጨናግፏል፤ ምርጫው ለበለለጠ ቀውስና ደም መፋሰስ ስለሚዳርገን ከዚያ በፊት ውይይት እናድርግ የሚሉ የማይጨብጥ ምኞትና ህልም ከማስተጋባት ውጭ ለዴሞክራሲ ሥርዓት መሠረት ሊጥል የሚችለውን የሽግግር ሂደት ሀሳብ ለመቀበል ፍላጎት ሲያሳዩ አይታይም።

ዴሞክራሲያዊ የሽግግር ሂደት ከአምባገነን ሥርዓት ወደ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት የሚያሸጋግር፤ የአምባገነን ሥርዓት የመጨቆኛ መሳሪያዎችን አስወግዶ ለእውነተኛው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሠረት የሚጣል፤ ብቸኛው መንገድ ነው። ዴሞክራሲያዊ የሽግግር ሂደት በተለያዩ አገራዊ ጉዳዮች ላይ የተለያዩ አቋሞች፤ አመለካከቶችና ሀሳቦች የያዙ ኃይሎች በውይይትና በድርድር ብሔራዊ ስምምነትና መግባባት ላይ እንዲደርሱ መድረክ የሚሰጥ፤ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሠረት የሆኑት አካሎችና ተቋሞች እንዲጠናከሩ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር፤ በዜጎች ላይ የደረሱ በደሎችን፤ ወንጀሎችን ወዘተ... በእርቅና በመግባባት መንፈስ የሚያስተናግድ ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል የሚሳተፍበት ብቸኛው መንገድ ነው።

ዴሞክራሲያዊ የሽግግር ሂደት ጊዜያዊ መንግሥት፤ የአንድነት መንግሥት፤ የአደራ መንግሥት ወዘተ... ከሚሉት የተለየ ነው። ብዙውን ጊዜ እነዚህ የአስተዳደር አካላት የሚመሠረቱት በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ አንድ በሕዝብ ምርጫ ወደ ሥልጣን የመጣ ፓርቲ ከሕዝብ ወይም ከፓርላማ አባላት ድጋፍ ሲያጣና በራሱ ፈቃድ ሥልጣን ሲለቅ መንግሥታዊ አስተዳደሩ በአገራዊ ምርጫ በሌላ ፓርቲ እስኪተካ ድረስ በጊዜያዊነት የአስተዳደር ተግባሮችን ለማከናወን እንዲቻል ነው። አምባገነን አገዛዝን አስወግዳ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመገንባት ዝግጁ ለሆነች አገር ግን የሽግግር ሂደት ጠቃሚ ብቻ ሳይሆን የግድ አስፈላጊም ነው።

በአገር ውስጥ አምባገነኑ ኃይል የተከላቸውን ስር የሰደዱ ምስቅልቅል ሁኔታዎች አስወግዶ ለእውነተኛው የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መሠረት ለመጣል የሽግግር ሂደት ቢያንስ ከሶስት እስከ አራት ዓመት ጊዜ ይወስዳል። ነገ ለአምባገነንትና ለቀውስ ምቹ የሆነ የሆይ ሆይታ ተግባር ከመፈጸም ጊዜ ወስዶ መሠረቱ የማይነቃነቅና ለማንኛውቸውም አምባገነን ኃይል ጥቃት የማይበገር ጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት መገንባት በማናቸውም መለኪያ ተመራጭ ይሆናል።

ቀደም ብሎ በተሰራጨ የዴሞክራሲያ ዕትም ላይ እንደተገለጸው የሽግግር ሂደት ሁሉንም የኅብረተሰብ ክፍሎች - የፖለቲካ ፓርቲዎች፤ የሙያ ማኅበሮች፤ የብዙሃን ድርጅቶች፤ ታዋቂና አገር ወዳድ ግለሰቦች፤ ከየአካባቢው የተወከሉ ዜጎችን ወዘተ... የሚያሳትፍ የውይይት የድርድርና የስምምነት መድረክ ነው። የሽግግር ሂደት ዓላማውም ሆነ ተግባሩ የሽግግር መንግሥት ማቋቋም ብቻ አይደለም። በእርግጥ በሽግግሩ ወቅት አገሪቱ እንደአገር መቀጠል ስላለባትና መንግሥታዊ የአስተዳደር ተግባሮች መከናውን ስላለባቸው የአስተዳደር አካል ያስፈልጋታል። ይህን ኃላፊነት በስምምነት በአገር ወዳድነታቸውና በሙያቸው ብቃት ላላቸው ሰዎች መስጠት ይቻላል.። የሽግግር ሂደቱ ዋና ዓላማና ተግባር ግን በውይይት፤ በንግግር፤ በድርድርና በስምምነት ለአገሪቱ ዋና ዋናና መሠረታዊ ችግሮች ዘላቂ የሆኑ አስተዳዳራዊ፤ መዋቅራዊና ሕጋዊ መፍትኄ መስጠት ነው። ለዚሁም ሁሉም የኅብረተሰብ ክፍል የሚወከሉበትና የሚሳተፉበት የሽግግር ጉባዔ ወይም ሸንጎ መመሥረት ቀዳሚ ተግባር ነው።

ይህ የሽግግር ጉባዔ ወይም ሸንጎ በስምምነት በሚደረስበት የጊዜ ሰሌዳ የሚያከናውናቸው ተግባሮች በርካታ ቢሆኑም ሕገ መንግሥቱን በአዲስ መልክ መመርመርና ማሻሻል፤ መንግሥታዊ ተቋሞች ለሕዝብ እና ለአገሪ ተጠሪ የሚሆኑበትን መንገድ ማመቻቸት፤ በኅብረተሰብ ውስጥ ሰላምና እርቅ እንዲሰፍን እንቅስቃሴ ማድረግና በሕዝብ የተመረጠ ፓርቲ ወደ ሥልጣን የሚወጣበትን መንገድ መቀየስ ዋና ዋናዎቹ ናቸው።

በዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ውስጥ በፈቃደኛነት በአንድ ላይ ለመኖር ለወሰነ ኅብረተሰብ ሕገ መንግሥት የቃል ኪዳን ሰነድ እንደመሆኑ መጠን በአንድ አገር ውስጥ የሚገኙ ዜጎች በይዘቱ ላይ አጠቃላይ ስምምነት ወይም ብሔራዊ መግባባት ሊኖራቸው ይገባል። አገራችን የተለያዩ ቋንቋዎች፣ ባህል፤ ሃይማኖት ወዘተ... ያሏቸው ብሔርና ብሔረሰቦች በአንድነት የኖሩባት እና የሚኖሩባት አገር ነች። በአገራዊ ደረጃ የሚቀረጸው ሕገ መንግሥት በአንድ በኩል የእነዚህን የተለያዩ የሕዝብ ወገኖች፤ ፍላጎትና ጥቅም የሚያስተናግድ መሆን ሲገባው በሌላ በኩል ማንኛውም ዜጋ በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል በነፃነት የመንቀሳቀስ የመኖር፤ ሀብት የማፍራት ሆነ ያሻውን የመምረጥ መብቱ የማይገረሰስ መሆኑ ሕገ መንግሥቱ ሊያረጋግጥለት ይገባል። በአሁኑ ወቅት በተግባር ላይ የዋለው ሕገ መንግሥት የወያኔ ቡድን ወደ ሥልጣን ሲመጣ በወያኔና በግብረ አበሮቹ ትብብር የተረቀቀ፤ በሕዝብ ዘንድ ነፃ ውይይት ሳይካሄድበት በተጽዕኖ የፀደቀ፣ ለ 28 ዓመታት የወያኔ አምባገነን አገዛዝ መሣሪያ ሆኖ ያገለገለ መሆኑ ግልጽ ነው። በሕገ መንግሥቱ በሰፈሩት የተለያዩ ጉዳዮች - በአንቀጽ 39 ውስጥ በሰፈረው የብሔር/ብሔረሰቦች የመገንጠል መብት ጉዳይ፤ በመንግሥት አወቃቀር፤ በምርጫ ሥርዓት፤ በምርጫ ቦርድ አሰያየም፤ በሰንደቅ ዓላማ፤ በብሔራው ቋንቋ፤ በዋና ከተማ ሌሎች የቻርተር ከተሞች የማንነት መብት እንዲሁም በሌሎች ዋና ዋና ጉዳዮች ላይ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች የተለያዩና ተጻራሪ የሆኑ አመለካከቶችና አቋሞች በመያዛቸው እነዚህ በውይይትና በድርድርና እንዲሁም በውሳኔ ሕዝብ አስታርቆ ብሔራዊ መግባባት ላይ መድረስ የግድ አስፈላጊ ይሆናል። ይህ በሽግግሩ ወቅት መከናወን ካለባቸው የተለያዩ ጉዳዮች አንዱና ቀዳሚው ነው።

ብዙኀኑ መብቱንና ጥቅሙን የሚያስጠብቅበትና ወሳኝነቱን የሚያረጋግጥበት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት በአገሪቱ ውስጥ ያሉ መንግሥታዊ ተቋሞች አካሎች ነፃና ገለልተኛ ሳይሆኑ ተግባራዊ ሊሆን የሚችልበት እድል የመነመነ ነው። የአገሪቱ ወታደራዊና የፀጥታ ተቋሞች፤ የፍርዱ ተቋም፤ የአስተዳድር ተቋሞችና አካሎች ፍጹም ገለልተኛና ከማንኛውም የፓርቲ ሆነ የቡድን ተጽእኖና ቁጥጥር ነፃ መሆን አለባቸው። የአገርና የሕዝብን ነፃነት ለመጠበቅ፤ የሕግ የበላይነት ለማስከበርና የአገሪቱን ሁለንተና የአስተዳደር ክንዋኔዎችን ለመፈጸም ከመላው ሕዝብ ኃይልና ሥልጣን የተሰጣቸው ተቋሞችና አካሎች ነፃና ገለልተኛ ካልሆኑ የግለሰብም ሆነ የቡድን አምባገነን ገዥዎች መጠቀሚያ ሆነው ሕዝብን ሊበድሉና ሊጨቁኑ እንደሚችሉ የአገራችንም ሆነ የሌሎች በርካታ አገሮች ተመክሮዎች በግልጽ የሚመሰክሩ ናቸው። በአሁኑ ወቅት በአገሪቱ የሚገኙት መንግሥታዊ መዋቅሮች ነፃና ገለልተኛ እንዲሁም ተጠሪነታቸው ለአገር እና ለሕዝብ ብቻ እንዲሆን የማስቻልና እንዲሁም ተጠሪነታቸውን በዘላቂነት የሕዝብ ለማድረግ የሚያስፈልገውን የቁጥጥር ሥልትና ዘዴ የመትለም ተግባር በሽግግር ሂደት በሚቋቋመው የሽግግር ጉባዔ ወይም የሽግግር ሸንጎ ይከናውናል።

በ27 ዓመታት የወያኔ የሥልጣን ዘመን እንዲሁም ላለፉት ሁለት ዓመታት በተካሄዱት ጥገናዊ ለውጦች በወገኖች ላይ በርካታ በደሎች ደርሰዋል፤ ወንጀሎች ተፈጽመዋል። ወንጀለኞች ጥፋታቸውን አምነው፤ ለቅጣት ዝግጁ የሚሆኑበትና ይቅርታ የሚጠይቁበት፤ ተበዳዮችም ይቅርታ የሚሰጡበት እንዲሁም ጥፋታቸው ከባድ የሆነ ለፍርድ የሚቀርቡበት የሰላምና የይቅርታና የእርቅ እንቅስቃሴ የሚካሄደው በሽግግር ሂደት ነው። የሽግግሩ ምክር ቤት ይህ ተግባር የሚያከናውነው የሰላም እና እርቅ ኮሚሽን በማቋቋም ነው። የኮሚሽኑም ተግባር እና ተልዕኮም የበቀል እርምጃ ለመውሰድ ሳይሆን እንቅስቃሴው ለተከታታይ ትውልዶች ትምህርት ሆኖ ወንጀሉ እንዳይደገም ለማድረግ ነው። እዚህ ላይ መዘረዘሩ አስፈላጊ ባይሆንም በሽግግሩ ሂደት የሚከናወኑ ሌሎች በርካታ ጉዳዮች ይኖራሉ።

በአሁኑ ወቅት በአገራችን ጎላ ብለው የሚታዩ ችግሮችን ለማስወገድም ሆነ በዘላቂነት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን ለመትከል የሽግግር ሂደትን እውን ከማደረግ ሌላ የተሻለ አማራጭ የለም። በእርግጥ ጽንፈኛ ብሔረተኛነት በነገሠበት፤ የእኛ፤ የሁላችንም ከሚለው ይልቅ የእኔ፣የቡድኔ ወዘተ… የሚለው ስሜት በበረታበት፤ ልዩነትና ጥላቻ መድረኩን በያዙበት፤ መደማመጥ በጠፋበት ሁኔታ የሽግግር ሂደትን ተግባራዊ ለማደረግ ፈተና መሆኑ ግልጽ ነው። የሽግግር ሂደት የተጨባጩን ሁኔታ ምንነት መገንዘብን፣ ልበ ሰፊ መሆንን፣ አርቆ አሳቢነትን ይጠይቃል። በዛሬዋ ኢትዮጵያ ማንም ግለሰብ ሆነ ቡድን፣ ብሔር ሆነ ብሔረሰብ የሌላውን መብት፣ ጥቅምና ፍላጎት ረግጦ ሊሄድ የማይችል መሆኑን መረዳት ይኖርበታል። በተግባር ለማዋል ቢጥር እንኳ ተከታታይና ማለቂያ የሌለው የእርስ በርስ ፍጅት ሊያስከትል እንደሚችል መገንዘብ የግድ ነው። ስለሆነም በአርቆ አሳቢነትና በልበሰፊነት ችግሮች በውይይት በድርድርና በመግባባት ሊፈቱ የሚችሉበት የሽግግር ሂደት እውን እናድርግ በማለት ለሁሉም የሕዝብ ወገኖች ጥሪያችንን እናስተላልፋለን።

**ሁላችንም በኅብረት፤ በአንድነት በእኩልነት ለምንኖርባት ኢትዮጵያ የጋራ ድርሻችንን እንወጣ !!!**

**ኢትዮጵያ ነበረች፣ አለች፣ ትኖራለች !!!**